የሰ/መ/ቁ. 111094

ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-**ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

**አመልካች፡-** መርዕድ ታደሰ ህንፃ ስራ ተቋራጭ የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ተስፋማርያም ደርብ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከስራ መሪ የስራ ስንብት ጋር ተያይዞ የተነሳ የስራ ክርክር ጉዳይን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ በ15/02/2006 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ፣ ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ከ23/02/2002 ዓ.ም ጀምሮ ብር 5,500 / አምስት ሺህ አምስት መቶ / የወር ደመወዝ እያገኙ በንብረት ክፍል እና በዋናው መስሪያ ቤት በአስተዳደር የስራ መደብ ላይ ሲሰሩ መቆየታቸውን፣ ከሳሽ ከዚህም በተጨማሪ አድመር ኢነርጂ ባላንስ ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሚባል ድርጅትም ሲሰሩ መቆየታቸውን ተከሳሽ የነሐሴ ወር 2005 ዓ.ም እና የመስከረም ወር 2006 ዓ.ም ደመወዝ ሳይከፍላቸው ካለምንም ጥፋት የስራ ውላቸውን ያቋረጠባቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሽ ያልተከፈላቸውን የሁለት ወር ደመወዝ፣ የስራ ስንብት፣ የካሳ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂ ጊዜ ክፍያ፣ ክፍያ የዘገየበት እና የዓመት ፈቃድ ክፍያ በድምሩ ብር 75,536.26 እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ በበኩሉ በ04/04/2006 ዓ.ም በሰጠው መልስ ከሳሽ ከ24/12/2003 ዓ.ም ጀምሮ አድመር ኢነርጂ ባላንስ ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወደሚል ድርጅት የተዛወሩ በመሆኑ ተከሳሽን በጉዳዩ የማያገባው መሆኑን የሚገልጽ መቃወሚያ ካስቀደመ በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ከሳሽ በተመሳሳይ ጊዜ በሁለቱም ድርጅቶች ስራ ሰርቻለሁ በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ከሳሽ ከ27/11/2005 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ገበታቸው ላይ ባለመገኘታቸው ከስራ የቀሩበትን ምክንያት ይዘው እንዲቀርቡ ቀጣሪው ድርጅት በ03/12/2005 ዓ.ም በደብዳቤ የገለፀላቸው ቢሆንም ሪፖርት ባለማድረጋቸው ከስራ የተሰናበቱት በራሳቸው ፈቃድ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ክሱን ከሰማ እና የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር ከመረመረ በኃላ ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽ ከ24/12/2003 ዓ.ም ጀመሮ አድመር ኢነርጂ ባላንስ ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወደሚባል ድርጅት ተዛውሯል

በማለት የተከራከረ ቢሆንም ከሳሽ የሁለቱ ድርጅቶች ስራ አስኪያጅ አንድ ሰው በመሆኑ ምክንያት በቃል በተሰጣቸው ትዕዛዝ ለሌላኛው እህት ኩባንያ ጭምር ይሰሩ የነበረ ከመሆኑ ውጪ የዝውውር ደብዳቤው እንዳልደረሳቸው ክደው የተከራከሩ መሆኑን፣ ከሳሽ በርግጥም የተዛወሩ ስለመሆኑ የዝውውር ደብዳቤውን ፈርመው የተቀበሉበትን ሰነድ ተከሳሽ ድርጅት አቅርቦ ማስረዳት አለመቻሉን ከሳሽ የሁለቱ ድርጅቶች ስራ አስኪያጅ በሆኑት ግለሰብ በተሰጣቸው የቃል ትዕዛዝ መሠረት ለሁለቱ ድርጅቶች ጥቅም ሲሰሩ መቆየታቸውም ሆነ ደመወዝ ሲከፈላቸው የነበረው በአድመር ኢነርጂ ባላንስ ስም በተዘጋጀ ፔሮል መሆኑ የተከሳሽ ድርጅት ሰራተኛ አይደሉም የሚያሰኛቸው አለመሆኑን፣ ተከሳሽ ድርጅት በደፈናው ክሱ አይመለከተኝም ከማለት በቀር ከሳሽ የተሰናበቱት በሕግ አግባብ ስለመሆኑም ሆነ በከሳሽ ስለተጠየቁት ክፍያዎች ያቀረበው የማስተባበያ ክርክር አለመኖሩን በዝርዝር ገልጾ ተከሳሽ ድርጅት፡-

1. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2574/2/ መሠረት የካሳ ክፍያ የሶስት ወር ደመወዝ ብር 14,046
2. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2571/2/ እና /3/ መሠረት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የሁለት ወር ደመወዝ ብር 9,364
3. የ34 ቀን የዓመት ፈቃድ ክፍያ ብር 5,306
4. ያልተከፈለ የሁለት ወር ደመወዝ ብር 9,364

በድመሩ ብር 38,080 /ሰላሳ ስምንት ሺህ ሰማንያ / ለከሳሽ እንዲከፍል እና በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2588/1/ መሠረት የተዘጋጀ የስራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይግባኙን የተመለከተው የፌዴራል ከፈተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርመሮ ተጠሪው የሰበር ተጠሪ እህት ኩባንያ ወደሆነው አድመር ኢነርጂ ባላንስ ተዛውሮ ይሰራ እንደነበረ እና ደመወዝም ሲከፈለው የነበረው ከዚያው ከተዛወረበት ድርጅት እንደነበረ ተረጋግጦ እያለ የሁለቱም ድርጅቶች ስራ አስኪያጅ አንድ ሰው ነው በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የመከራከሪያ ነጥቦች ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉይዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪ ከ23/02/2000 ዓ.ም ጀምሮ የተቀጠሩት በአመልካች ድርጅት መሆኑ ያልተካደ ሲሆን ከ24/12/2003 ዓ.ም ጀመሮ አድመር ኢነርጂ ባላንስ ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወደሚል ድርጅት ተዛውረዋል በማለት አመልካች የተከራከረ ቢሆንም ዝውውር መደረጉ በተጠሪው የተካደ እና አመልካቹም ይህንን ነጥብ ማስረዳት ያልቻለ መሆኑን እንዲሁም ተጠሪ ለሁለቱም ድርጅቶች ጥቅም እንዲሰሩ የተደረገውም ሆነ ፔሮሉ ከጊዜ በኃላ በአድመር ኢነርጂ ባላንስ ስም እንዲዘጋጅ የተደረገው በአመልካች ድርጅት ስራ አስኪያጅ የቃል ትዕዛዝ መሆኑን ተጠሪው በስር ፍርድ ቤት ገልጸው መከራከራቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ይግባኙን የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

የተሰጠውን ውሳኔ ሊያጸና የቻለው ተጠሪው ተዛውረዋል ከተባለበት ቀን በኃላም በተለያዩ ጊዜያት አመልካች ድርጅትን ወክለው በጨረታ የመሳተፍ እና መሰል ተግባራትን ሲያከናውኑ የነበሩ ስለመሆኑ በተጠሪው በኩል የቀረበውን ክርክር አመልካች ክዶ ያልተከራከረ መሆኑን እና ተጠሪው ከስራ የተሰናበቱት ከ27/11/2005 ዓ.ም ጀመሮ በስራ ገበታቸው ላይ ባለመገኘታቸው ነው በማለት አመልካች የተከራከረ ቢሆንም ተጠሪው ነሐሴ 15 እና ነሐሴ 17 ቀን 2005 ዓ.ም በአመልካች ድርጅት እና በአድመር ድርጅት ተወክለው የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ እንደነበረ የሚያረጋግጡ ደብዳቤዎች በእጃቸው እንደሚገኙ ገልጸው ተጠሪው ያቀረቡትን ክርክር አመልካች ያላስተባበለ መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ ተጠሪው በሰበር መልሳቸው ያቀረቡትን ተመሳሳይ የክርክር ነጥቦች በዝምታ ከማለፍ በቀር አመልካች በመልስ መልሱ የማስተባበያ ክርክር ያላቀረበባቸው መሆኑንም መዝገቡ ያመለክታል፡፡

በመሰረቱ የስራ ውል ማለት ከተዋዋዮቹ ወገን አንዱ ሰራተኛው ለሌላው ወገን ለአሰሪ አንድ ግዙፍነት ያለው ወይም የአዕምሮ ስራ በተወሰነ ወይም ባልተወሰነ ጊዜ ውስጥ አሰሪው ሊከፍለው በተገደደበት አንድ ደመወዝ በርሱ አገልግሎትና በርሱ መሪነት ስራውን ለማከናወን ግዴታ የሚገባበት ውል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2512 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚህ ሁኔታ የስራ አገልግሎት ውሉ የተደረገው በአመልካች እና በተጠሪው መካከል መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪው በተለመደው የአሰራር አግባብ ወደ እህት ኩባንያው እንዲዛወሩ ሳይደረግ የአመልካች ስራ አስኪያጅ በተመሳሳይ ሁኔታ በስራ አስኪያጅነት ለሚመሩት ሌላ ድርጅት ተጠሪው ግዴታ ከገቡበት የአመልካች ስራ ውጪ እንዲሰሩ ማድረጋቸው እና መደበኛ ዝውውር ሳይደረግ ፔሮሉ በእህት ኩባንያ ስም እንዲዘጋጅ መደረጉ ተጠሪው ከአመልካች ጋር በሕግ አግባብ ያደረጉትን የስራ ውል ተፈፃሚነት እና ውጤት ሊያስቀር የሚችል ተደርጎ መወሰድ የሚገባው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 86208 በ26/06/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 150968 በ28/05/2007 ዓ.ም በፍርድ የፀናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 117526 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ29/07/2007 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶአል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

**ወ/ከ**